የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ — ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 7
ADDIS ABABA - 8th December, 2000

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፭/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በኤርትራ መንግሥታት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ .......................... ገጽ ፲፬፻፴፯

## CONTENTS

Proclamation No. 225/2000
Peace Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Eritrea Ratification Proclamation .......................................... Page 1437

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፭/፲፱፻፺፫
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በኤርትራ መንግሥታት መካከል የተደረገውን የሰላም ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኤርትራ መንግሥት መካከል የነበረውን ግጭት ለማስቆም በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በሌሎች አደራዳሪ ሦስተኛ ወገኖች አማካኝነት የተደረሰውን የሰላም ስምምነት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲያጸድቀው የቀረበ በመሆኑ፣

የተደረሰው ስምምነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብርና ለአካባቢያችን ሰላም መስፈን ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረው በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በኤርትራ መንግሥታት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፭/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO.225/2000*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE PEACE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF ERITREA*

WHEREAS, the Peace Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Eritrea, through the conciliation of the OAU and other third parties, has been submitted to be ratified by the House of Peoples' Representatives;

WHEREAS, the Agreement reached at by the two Governments is found to be of paramount importance in protecting the national interests of Ethiopia and peace of the Region;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives has ratified said Agreement at its session held on the 8th day of December, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia , it is hereby Proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Peace Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Eritrea Ratification proclamation No.225/2000".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ይህንን ስምምነት ከኤርትራ መንግሥት ጋር እንዲፈራረም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተስማምቶበታል።

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ የሁለቱ አገሮች መንግሥታት ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The House of Peoples' Representatives, having ratified the Agreement has delegated the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to sign the Peace Agreement with the Government of the State of of Eritrea.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the date on which the Agreement is signed by the Governments of the two States

Done at Addis Ababa, this 8th day of December, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE